ግብጽ አረብ ሪፐብሊክ     ረመዳን 7/1443 ሂ.

የአውቃፍ ሚኒስቴር     አፕሪል 8/2022 ግ.

# የጾም እምነታዊና ስነ ምግባራዊ ጎኑ

ምስጋና ሁሉ በተከበረው መጽሐፉ

{وَسَارِعُوا إِلَى مَغْفِرَةٍ مِنْ رَبِّكُمْ وَجَنَّةٍ عَرْضُهَا السَّمَاوَاتُ وَالْأَرْضُ أُعِدَّتْ لِلْمُتَّقِينَ * الَّذِينَ يُنفِقُونَ فِي السَّرَّاءِ وَالضَّرَّاءِ وَالْكَاظِمِينَ الْغَيْظَ وَالْعَافِينَ عَنِ النَّاسِ وَاللَّهُ يُحِبُّ الْمُحْسِنِينَ}

ለአለው ለዓለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የአንቀጾቹ ትርጉም፡

(ከጌታችሁ ወደ ኾነችም ምሕረትና ስፋትዋ እንደ ሰማያትና ምድር ወደ ኾነች ገነት አላህን ለሚፈሩ የተዘጋጀች ስትኾን ተቻኮሉ፡፡ ለእነዚያ በድሎትም ኾነ በችግር ለሚለግሱት፣ ቁጭትንም ገቺዎች ከሰዎችም ይቅርታ አድራጊዎች ለኾኑት (ተደግሳለች)፡፡ አላህም በጎ ሠሪዎችን ይወዳል፡፡) ማለት ይሆናል፡፡

አጋር የሌለው ብቸኛ አላህ እንጅ የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመስክራለሁ፡፡ ሰይዳችንና ነብያችን ሙሐመድ የእሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! የምህረት እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና እስከ እለተ ቂያማ ድረስ በመልካሙ መንገድ ለተከተሏቸው አውርድ፡፡

ከዚህም በመቀጠል

አላህ (ዐ.ወ.) ጾምን ግድ ያደረገው ለላቁ አለማዎችና ለተከበሩ ጥበባት ነው፡፡ ጾም የእምነትና የስነ ምግባር መማሪያ ትምህርት ቤት ነው፡፡ የተከበረው ቁርኣንን ጠለቅ

ብሎ የሚመራመር ሰው አላህ (ሱ.ወ.) የጾምን ዋና አላማ እንድህ በማለት የገለጸው መሆኑን በቀላሉ ሊገነዘብ ይችላል፡፡

{يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا كُتِبَ عَلَيْكُمُ الصِّيَامُ كَمَا كُتِبَ عَلَى الَّذِينَ مِنْ قَبْلِكُمْ لَعَلَّكُمْ تَتَّقُونَ}

(እናንተ ያመናችሁ ሆይ ጾም በነዚያ ከናንተ በፊት በነበሩት (ሕዝቦች) ላይ እንደ ተጻፈ በናንተም ላይ ተጻፈ (ተደነባ) ልትጠነቀቁ ይከጀላልና፡፡) እዚህ ላይ ጥንቃቄ የሚለው ቃል ሁሉንም የደግ ነገር ባሕርይዎች ያከተተ መሆኑን ልናጤን ይገባል፡፡ ስለዚህም በተከበረው ቁርኣን ጾም ብዙውን ጊዜ ከተለያዩ የእምነትና የስነ ምግባር እሴቶች ጋር ተቆራኝቶ ተጠቅሷል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{لَيْسَ الْبِرَّ أَنْ تُوَلُّوا وُجُوهَكُمْ قِبَلَ الْمَشْرِقِ وَالْمَغْرِبِ وَلَكِنَّ الْبِرَّ مَنْ آمَنَ بِاللَّهِ وَالْيَوْمِ الْآخِرِ وَالْمَلَائِكَةِ وَالْكِتَابِ وَالنَّبِيِّينَ وَآتَى الْمَالَ عَلَى حُبِّهِ ذَوِي الْقُرْبَى وَالْيَتَامَى وَالْمَسَاكِينَ وَابْنَ السَّبِيلِ وَالسَّائِلِينَ وَفِي الرِّقَابِ وَأَقَامَ الصَّلَاةَ وَآتَى الزَّكَاةَ وَالْمُوفُونَ بِعَهْدِهِمْ إِذَا عَاهَدُوا وَالصَّابِرِينَ فِي الْبَأْسَاءِ وَالضَّرَّاءِ وَحِينَ الْبَأْسِ أُولَئِكَ الَّذِينَ صَدَقُوا وَأُولَئِكَ هُمُ الْمُتَّقُونَ.

(መልካም ሥራ ፊቶቻችሁን ወደ ምሥራቅና ምዕራብ አቅጣጫ ማዞር አይደለም፡፡ ግን መልካም ሥራ በአላህና በመጨረሻው ቀን፣ በመላእክትም፣ በመጻሕፍትም፣ በነቢያትም፣ ያመነ ሰው ገንዘብንም ከመውደዱ ጋር ለዝምድና ባለቤቶችና ለየቲሞች ለምስኪኖችም፣ ለመንገደኞችም፣ ለለማኞችም፣ ለጫንቃዎችም (ማስለቀቅ) የሰጠ ሰውና ሶላትንም ደንቡን ጠብቆ የሰገደ፣ ዘካንም የሰጠ፣ ቃል ኪዳንም በገቡ ጊዜ በኪዳናቸው የሞሉ (ሰዎች ሥራ) ነው፡፡ በችግር በበሽታና በጦር ጊዜም ታጋሾችን (እናወድሳለን)፡፡ እነዚህ እነዚያ እውነትን የያዙ ናቸው፡፡ እነዚያም ተጠንቃቂዎቹ እነርሱ ናቸው፡፡)

ከጾም የእምነትና ስነ ምግባር ጎኖች አንደኛው የቁጥጥር እሴት ነው፡፡ ጾም ከአንድ ባሪያና ከፈጣሪው መካከል የሚከውን፣ ከአላህ በስተቀር ማንም ሊያውቀው የማይችል ምስጥራዊ ተግባር ነው፡፡ ጾም የሰው ልጅ የምስጢርም ሆነ የግልጽ ተግባሩን አለህ (ሱ.ወ.) የሚያወቅ መሆኑን የሚያረጋግጥ ለመሆኑ መረጃ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{وَمَا تَكُونُ فِي شَأْنٍ وَمَا تَتْلُو مِنْهُ مِنْ قُرْآنٍ وَلَا تَعْمَلُونَ مِنْ عَمَلٍ إِلَّا كُنَّا عَلَيْكُمْ شُهُودًا إِذْ تُفِيضُونَ فِيهِ وَمَا يَعْزُبُ عَنْ رَبِّكَ مِنْ مِثْقَالِ ذَرَّةٍ فِي الْأَرْضِ وَلَا فِي السَّمَاءِ وَلَا أَصْغَرَ مِنْ ذَلِكَ وَلَا أَكْبَرَ إِلَّا فِي كِتَابٍ مُبِينٍ)

(ሙሐመድ ሆይ!) በማንኛውም ነገር ላይ አትሆንም፣ ከርሱም ከቁርኣን አታነብም፣ ማንኛውንም ሥራ (አንተም ሰዎቹም) አትሠሩም በገባችሁበት ጊዜ በናንተ ላይ ተጠባባቂዎች ብንሆን እንጂ፡፡ በምድርም ሆነ በሰማይ የብናኝ ክብደት ያክል ከጌታህ (ዕውቀት) አይርቅም፡፡ ከዚያም ያነሰ የተለቀም የለም፤ በግልጹ መጽሐፍ ውስጥ የተጻፈ ቢሆን እንጂ፡፡)

የጾም ምንዳ ከአላህ በስተቀር ልኩን የማያውቀው እጅግ ታላቅ የመሆኑ ምስጢር የቁጥጥር እሴት ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (የሁሉም ሰው ምንዳ እጥፍ ድርብ ይሆናል፡፡ አንድ መልካም ስራ አስር እጥፍ እንዳንዴም እስከ ሰባት መቶ እጥፍ ይደርሳል፡፡ ታላቁ አላህ ደግሞ እንድህ ብሏል፡ ጾም ሲቀር እሱ የኔ ነው እኔ በራሴ ምንዳውን እሰጥበታለሁ፡፡ እሱ ለኔ ብሎ ከስሜቱና ከምግቡ ታቅቧልና)፡፡ በጾሙ አላህ የሚቆጣጠረው መሆኑን የሚያምን ጾመኛ በረመደንም ሆነ ከረመዳን ውጭ በስራው፣ በምርቱና በሌሎቹም ተግባራቱ አላህ የሚቆጣጠረው መሆኑን ሊገነዘብ ይገባል፡፡

ጾም በማንኛውም መልኩ ትእግስትን የምንማርበት ተግባር ነው፡፡ በጾም ወቅት ኢባዳዎችን በማድረስ፣ እርም ነገሮችን በመከልከልና ከስሜት በመታቀብ ታጋሾች መሆን ይኖርብናል፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ረመዳንን የትግስት ውር የሚል ስያሜ ሰጥተውታል፡፡ እንድህም ብለዋል፡ (የትእግስትን ውርና በየወሩ ሦስት ቀናት መጾም አመትን ሁሉ እንደመጾም ይቆጠራል)፡፡ በመሆኑም ጾመኛ ሰው ቁጭቱን በማመቅ፣ በዳዩን ይቀር በማለት፣ ለከለከለው በመስጠትና መጥፎ ለፈጸመበት መልካም በመስራት በትግስት ጸባይ ሊታነጽ ይገባል፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (የአንዳችሁ የጾም ቀን በሚሆንበት ወቅት በዚያን ቀን ጽያፍ አይናገር፣ ድምጹንም ከፍ አያድርግ፡፡ አንድ ሰው ቢሳደበውና ቢታገለው እኔ ጾመኛ ሰው ነኝ ይበል)፡፡

እንድሁም እውነተኛ ጾመኛ አይዋሽም፣ አያታልልም፣ አይክድም፣ አያምታታም፣ ማንንም ሰው አያማም፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ የሀሰት ቃልንና እሱን መፈጸመን ያልተወ ሰው ምግብና መጠጡን ለመተው አላህ ትርጉም አይሰጠውም)፡፡

****

ምስጋና ሁሉ ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የእዝነት መህረትና ሰላም የነብያትና የመልክተኞች መደምደሚያ በሆኑት በሰይዳችን ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ.) በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይውረድ፡፡

በጣም አስፈላጊ ከሆኑት የጾም አላማዎች መደጋገፍ፣ መተዛዘን፣ አንድ ሰው በአካባቢው ለአሉት ደሃዎችና እርዳታ ለሚስፈለጋቸው ሰዎች ሁኔታ ግንዛቤ ኖሮት ለነሱ ማዘኑ፣ እነሱን ማጽናናቱና የነሱን ጉዳይ ማውጣቱ የሚሉት ናቸው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) የትኛው እስልምና ነው በጣም ደጉ የሚል ጥያቄ በተጠየቁ ጊዜ እንድህ በማለት ነበር የመለሱት፡ (ምግብ ማብላትህ፡፡ ለምታውቀውም ለማታውቀውም ሰላምታ ማቅረበህ ነው)፡፡ የመደጋገፍ፣ የመተዛዘን፣ የቸርነትና የምግብ ማብላት ምንዳ በሌላው ጊዜ ታለቅ ነው ስንል፣ በረመዳን ያለው ምንዳ በጣም ታላቅ እንድሁም የአብሉ ትሩፋት በጣም የላቀ መሆኑ እውን ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (ጾመኛን ያስፈጠረ ከጾመኛው ምንዳ ምንም ሳይቀነስ የሱን ምንዳ ዓይነት ያገኛል)፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) አብደላህ ኢብን አባስ እንድህ ብለዋል፡ «ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) በደግ ነገር ከማነም የበለጠ ቸር ነበሩ፡፡ በጣም ቸርነታቸው የሚሰፋው ደግሞ በረመዳን ነበር»፡፡

ከጾም ትምህርት ቤት የእምነትንና የመልካም ምግባር ትሩፋትን መማራችን በሱም የጾምን ዋና አላማና ምንነቱን መገንዘባችን በጣም ጥሩ ውጤት ይኖረዋል፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ጃቢር ኢብን አብደላህ እንድህ ይላሉ፡ «ጾም በምትይዝበት ጊዜ መስሚያህና ማያህ ይጹሙ፣ ምላስህም ከሀሰትና ከወንጀል ተግባር ይታቀብ፡፡ ጎረቤት ከማስቸገርም ተቆጠብ፡፡ በጾምህ ቀንም ሞገስና እርጋታ ይኑርህ»፡፡

ጌታችን ሆይ ግብጽ ሀገራችንን እንድሁም መላ የአለም ሀገራትን ከመጥፎ ነገር ሁሉ ጠብቅልን፡፡ አሚን፡፡